Global Civic Movement for Change in Ethiopia

አለም-አቀፍ የሲቪክ ንቅናቄ ለለውጥ
በኢትዮጵያ

መጋቢት 17: 2003

# የወያኔ ከፍተኛ ባለሥልጣኖችን አጋልጠን በቃ ብለን እንመልሳቸው

በቃ! ገዬ! ባስ! ያዕከል! አሎኒ! ወታንደም! ጊደስ! ዲተም!

## የጋራ መግለጫ

የጎሰኛው ወያኔ ቡድን ተጠሪዎች ሰሞኑን በ 14 የሰሜን አሜሪካ ከተሞች በመዘዋወር በሕዝባችንና በሀገራችን ላይ ወያኔ የሚያራምደውን የግፍ አገዛዝ እንድንደግፍ፣ተጨማሪ የግፍና የአፈና ዘመን እንድናድስላቸው ጥሪ በማቅረብ ላይ ይገኛሉ። ወያኔዎች ሀገራችንን በመሣሪያ ሀይል 20 ዓመታት ቀጠቀጡ፤ጥላቻን ዘርተው፣ሀገር አራቁተው ኢትዮጵያን የግላቸው ርስት አደረጉ፤ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን አስርበው፣አፍነውና አደንቁረው መግዛታቸው ሲያንገበግበን የወንጀላቸው ተባባሪ ሊያደርጉን በድፍረት የተቀበሉን ጥሪ አደረጉ፤የኢትዮጵያ ሕዝብ የለውጥ ምጥ ውስጥ ባለበት፣ብሩህ ዘመን አሻግሮ ለማየት በሚጣደፍበት እነዚህን የጭለማ መልክተኞች በማሰፈር ተስፋውን የማለምልም ሐገራዊ ግዴታ አለብን፤ዶላር ፍለጋ የመጡትን ውርደት አሸክመን እንመልሳቸው፤በቃ እንበላቸው። የመለስ ቡድን በሕዝባችንና በሀገራችን ላይ የፈጸማቸውና በመፈጸም ላይ ያለውን በደሎችን በጥቂቱ ለማስታወስ ያህል፤

- ጎሳንና ቋዋንቋዋን መሠረት ያደረገ ፓሊሲ በመከተል ለዘመናት ተደጋግፎና ተባብሮ የኖረውን ሕዝብ በጎሪጥ እንዲተያይ፤ አንዱን ጎሳ በሌላው ላይ እነዲነሳ ማድረግ፤
- በ1997 የሕዝብ ምርጫ በሀይል ምርጫውን ነጥቆ ተቃዋሚዎችን ገድሎ አስሮና አስወግዶ የሕዝቡን ፍላጎት በኅይል ከማፈኑም በላይ በሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፈኞች ላይ ተኩስ በመክፈት 193 ወገኖቻችንን በአደባባይ መረሸኑ፤በጋምቤላ ከ400 በላይ ወገኖቻችንን መጨፍጨፉ፣በኦጋዴን፥በኦሮሚያ፣በአማራ ፣በደቡብ እና በሌሎች ክልሎችም በወገኖቻችን ላይ እልቂት ማንገሱ፤
- ወገኖቻችን ከመለስ የሰቆቃ አገዛዝ ለመላቀቅ በአራቱም የሀገራችን ማእዘኖች እየኮበለሉ ነው። በየበረሀውና በባህር በሚያደርጉአቸው አደገኛ ጉዞዎችም ህይወታቸውን እያጡ ነው
- የራሱንም ሕገ መንግሥት በሚፃረር መልኩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከ 50 ዓመት በላይ የታገለለትን መሠረታዊ የሰው ልጆች የመፃፍ የመናገርና የመሰብሰብ ነፃነት ገፎአል፤በተለይ ከምርጫ 97 ወዲህ የለየለት አፈናም አሰፍኗል፤
- እንደዚሁም ሕዝባችን ብዙ መስዋእትነት የከፈለበት የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ በአሁኑ ወቅት በወያኔ ቁጥጥር ሥር ሆኖ በተለይም ገበሬውን የወያኔ መንግስት ጭሰኛ ሆኗል፤

- ሕዝባችን እንደበቱ በመሣሪያ ሀይል ተዘግቶ፤ ብሶቱን በሰላማዊ መንገድ እንዳይገልጽ ታግዷል፤ ነጋዴው በነጻነት እንዳይገበያይ መለስ፤ባለቤቱና ግብረ አበሮቻቸው ዋጋ ተማኞች፤ አከፋፋዮች፤ ነጋዴዎችና ባለእንዱስትሪዎች ሆነው የሀገሪቱን ኤኮኖሚ እንደፈለጉት በማን አለብኝነት ተቆጣጥረዋል
- ከ3 ሚሊዮን የሚልቁ ዜጎቻችን አስቸኳይ እርዳታ በሚሹበት የሀገሪቱን ለም መሬቶች ለውጭ መንግሥታትና ባለሀብቶች ያለሕዝብ ፈቃድና ቁጥጥር እስከ 99 ዓመታት በሚቆይ ሊዝ በማከራየት ርሃብ በሀገራችን እንዲቀጥል የተሰማማ ዘራፊና አፋኝ ቡድን ነው፤

በሰሜን አፍሪካና በሌሎች አረብ ሀገሮች የተከሰተው ንቅናቄ ወደ ሀገራችን እየዘለቀ ቢሆንም፤ ወያኔ እያቀጣቀጠ ያለውን የሕዝብ ቁጣ ለማዳፈን የማያደርገው ጥረት የለም። መለስና ግብረ አበሮቹ እየተቀጣጠለ ያለውን ንቅናቄ ያቀሙ እየመሰላቸው በቅርቡ ገሙ ጎፋ ክፍለ ሀገር በሰምንት ወረዳዎች የተቀሰቀሰውን የሕዝብ ቁጣ ከፍተኛ ወታደራዊ ሀይል በመጠቀም ቀስቃሽ ናቸው ያላቸውን በመግደልና በማሰር ጨካኝ እርምጃ መውሰዱን የኢሳት ቴሌቪዥን በጊዜው ዘግቦታል። ከ 120 በላይ የሚሆኑ "ሽብር" ያስነሳሉ የሚላቸውን የራሱን ካድሬዎችና ቁጥራቸው ከ250 በላይ የሚደርሱ የመድረክ አባሎችን ሰሞኑን ሰብስቦ አሰሮ የት እንዳደረሳቸው አይታወቅም። እየተቀጣጠለ ያለውን የሕዝብ ቁጣ አቅጣጫ ለማስቀየር በማሰብም ከኤርትራ ጋር ጦርነት ለመጀመር በዝግጅት ላይ መሆኑን ከራሱ ከሥር ዓቱ ጋሻ ጃግሬዎች ሰምተናል።

የሀገር ቤቱን ተቃውሞ በመሣሪያ አፍኖ ይዞ የሚዘልቅ መስሎት ፣ በውጭ የሚገኘውንም ጠንካራ ተቃውሞ ለመግታት እነሆ በርካታ ተላላኪዎቹን በሰሜን አሜሪካ ከተሞች አሰማርቶአል። ለዚህም በዚህ በሰሜን አሜሪካ፤ በገንዘብና በጥቅማ ጥቅም የተገዙና የተደለሉ ግለሰቦችን አሰባስቦ ለመሰበክ ተዘጋጅቶአል። ቤት ለመሥሪያ ቦታ ይሰጣችሁዋል፤ በሀገሪቱ በኢንቨስትመንት መስክ እንድትሳተፉ መንግሥት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤ በማለት ጥቅም ፈላጊዎችን በመጋበዝ ለውጭው ዓለምም መልኩን ለማሳመር እየጣረ ነው። ይኅንኑ ውሸትና የሚያሳፍር ቅጥፈት ወያኔ በመደለያ መልክ ለብዙ ዓመታት ለውጭ ነዋሪዎች አቅርቦ አምነው ከተቀበሉት ብዙዎቹ ገንዘባቸውን በሰበብ አስባቡ ተነጥቀው በሃዘን ተመልሰዋል፤ ስለዚህም ወገኖቻችን እነዚህን ሀፍረተ ቢስ መልክተኞች ተባብረን በማሳፈር በቃ፤ ገዬ፤ ባስ፤ ያዕከል፤ አሎጊ፤ ወታንደም፤ ጊደስ፤ ዲታህ ብለን ወደ መጡብት እንመልሳቸው እንላለን።

## ኒው ዮርክ፡ ዋሽንግተን ዲሲ፡ ዳላስ፡ ላስ ቬጋስ፡ ሎስ አንጀለስ፡ ሳን ጆሴ ፡ ሚኒያፖሊስ ፡ ሲያትል ፡ አትላናታ ፡ ኦታዋ፡ ቶሮንቶ፡ ዴንቨር ፡ የተቃውሞ አስተባባሪ ግብረሃሎችና ቡድኖች

**ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያኖች ሲቪክ ንቅናቄ ለለውጥ**